# 1ኛ ጢሞቴዎስ (44)

## 1ኛ ጢሞቲዎስ መግቢያ ሃሳቦች

የጢሞቲዎስን መልዕክት ማን ጻፈው የሚለውን ጥያቄ ጸሃፊው ስሙን በደብዳቤው መጀመሪያ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ መሆኑንና፤ የተጻፈለት ሰው ደግሞ ጢሞቲዎስ እንደነበረ ቁ2 ይነግረናል፡፡

የሐዋ ሥራ 13፡1 ላይ ጳውሎስና በርናባስ በአንጾኪያ ቤ/ክ ተልከው እየተዘዋወሩ ወንጌልን በተለያዩ ሥፍራዎች ሲሰብኩ እንደነበረ ሥራ ምዕራፍ 13 እና 14 ላይ እንመለከታለን፡፡ ሐዋ ሥራ 15፡36 ላይ ስንመለከት ቀድሞ ሰበከው የተመለሱባቸውን ቦታዎች ተመልሰው ያመኑት ሰዎች እንዴት እንዳሉ እንዲሄዱ ጳውሎስ ለበርናባስ ሃሳብ ሲያቀርብና በሃሳቡ እንደተስማሙ እናያለን፤ ሆኖም ማን ከእነርሱ ጋራ ይሄድ የሚለው ጥያቄ በሃሳብ እንዲለያዩ ስላደረገ ሁለቱም ወደ ተለያየ አቅጣጫ መሄዳቸውን እናውቃለን፡፡

ሐዋ ሥራ 16፡1-3ትን ስናነብ ጳውሎስ ወደ ደርቤንና ልስጥራ ሄዶ በዚያ ጢሞቲዎስን እንዳገኘና የብዙ ወንድሞች ምስክርነት ስለሰማ ከእርሱ ጋራ ሊወስደው እንደፈለገ እናነባለን፡፡ ጳውሎስ በብዙ ሥፍራዎች (1ኛ ጢሞ 1፡2 18 1ኛ ቆሮ 4፡17) ጢሞቲዎስን ልጄ በማለት ይጠራዋል፤ ይህ አባባል ምናልባትም ጳውሎስና በርናባስ በመጀመሪያው የወንጌል አገልግሎታቸው ወንጌልን ሰብኮለት ወደ ጌታ እንደመጣና በዚህም ምክንያት በእምነት ልጄ ለሆነው ለጢሞቲዎስ የሚለውን አነጋገር እንደተጠቀም ይታመናል፡፡

ጳውሎስ ጢሞቲዎስን በልጅነቱ ብቻ ሳይሆን የሚያውቀው 1ኛ ቆሮ 4፡17፣ 1ኛ ቆሮ 1፡1፣ 1ኛ ተሰ 3፡2፣ ፊሊ 1፡1ድንና የመሳሰሉትን ክፍሎች ስንመለከት፤ እንደ ተወደደ ሰው፣ እንደ ታመነ ሰው፣ እንደ ወንድሙ፣ አብሮ እንደሚሰራ ሰራተኛ፣ እንደ ክርስቶስ ባሪያ አድርጎ ይመለከተዋል፡፡

ጳውሎስ በፊሊ 2፡19-21 ላይ የጢሞቲዎስን ለጌታና ለህዝቡ ያለውን ነገር ይናገርለታል፤ ስለሌሎች ህይወት በቅንነት የሚጨነቅ አገልጋይ እንደሆነ፣ የራሱን ነገር ሳይሆን የክርስቶስን ነገር የሚያስቀድምና የሚፈልግ ሰው እንደሆነ፣ ማንነቱን ያስመሰከረና ከጳውሎስ ሳይለይ ያገለገለ ታማኝ አገልጋይ ነው፡፡ ጳውሎስ የጢሞቲዎስን ብርቱ ጎኖች ብቻ የሚያውቅ ሳይሆን ደካማ ጎኑንም የተረዳለት እንደሆነ በ2ኛ ጢሞ 1፤7 እና በ1ኛ ቆሮ 16፡10 ላይ የፍርሃት ችግር እንደነበረበት እንረዳለን፡፡

የጢሞቲዎስን ማንነት ጳውሎስ መረዳቱ ብቻ ሳይሆን ጢሞቲዎስም የጳውሎስን ማንነት እንደሚያውቅና (2ኛ ጢሞ 3፡10-11) ጠለቅ ያለ የወንድማማዊ መተዋወቅ እንደነበራቸው እንገነዘባለን፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ሊሞት በተቃረበበት የመጨረሻ ሰዓቱ ሊያየውና ሊያነጋግረው የፈለገው ሰው ቢኖር ጢሞቲዎስ መሆኑን 2ኛ ጢሞ 4፡11 ግልጽ አድርጎ የሚያሳየን ሲሆን ይህም የመቀራረባቸውንና የፍቅራቸውን ጥልቀት ያስረዳናል፡፡ ጢሞቲዎስን ስንመለከት ከጳውሎስ ጋራ መጓዝ ከጀመረበት ሰዓት አንስቶ በሞት እስመሚለያዩ ድረስ የአገልግሎት ባልደረባና ረዳቱ እንደነበረ መረዳት አያስቸግረንም፡፡

ጳውሎስ ወደሮም በቶሎ እንዲመጣ በነገረው መሰረት ሄዶ ከመሞቱ በፊት ደርሶበት እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ የሚታወቅ ነገር የለም፤ ጢሞቲዎስን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱሳችን የሚነግረን ተጨማሪ ነገር ቢኖር በዕብ 13፡23 ላይ የዕብራዊያን ጸሐፊ ጢሞቲዎስ ታስሮ እንደተፈታና ከእርሱ ጋራ መጥቶ እንደሚያያቸው የነገራቸውን ብቻ እናውቃለን፡፡

ጳውሎስ በሐዋ ሥራ 20፡29-30 ላይ የፌሶንን ሽማግሌዎች አስጠርቶ የነገራቸው ነገር እውነት ሆኖ የሀሰት አስተማሪዎች በቤ/ክርስትያኒቱ ስለተነሱ ጢሞቲዎስን በዚያ ተቀምጦ ሁኔታዎችን እንዲያስተካክል ነው የነገረው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ጢሞቲዎስ ጳውሎስን ወክሎ በቆሮንቶስ (1ኛ ቆሮ 4፤17)፣ በፊሊጵስዩስ (ፊሊ 2፡19)፣ በተሰሎንቄ (1ኛ ተሰ 3፡2) እና እዚህም በአፌሶን (1ኛ ጢሞ 1፡3) ሐዋርያው ጳውሎስን ወክሎ ጊዜያዊ ተልዕኮ የሚፈጽም እንጂ የቤተ ክርስትያኒቱ ፓስተር ነበረ የሚለውን ሃሳብ የሚደግፍ ምንም ዓይነት ጥቅስ አላይም፡፡ በዚህም ሥፍራ ቋሚ እንዳልሆነ የምናውቀው በ2ኛ ጢሞ 4፡9 እና 4፡21 ላይ በቶሎ ወደ እርሱ እንዲመጣ ያሳስበዋል፡፡ ጌታ ይህንን ጥናት ለበረከት እንዲያደርግላችሁ ምኞቴ ብቻ ሳይሆን ጸሎቴም ነው፡፡

# ጥናት አንድ 1ኛ ጢሞ 1፡1-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጸሐፊው በዚህ ክፍል ውስጥ ራሱን የሚያስተዋውቀው በእግዚአብሄር አብና በኢየሱስ ክርስቶስ ትዕዛዝ ሐዋርያ የሆነ ሰው አድርጎ ሲሆን፤ መልዕክቱ የተጻፈለትን ሰው ደግሞ ‹‹በእምነት እውነተኛ ልጄ›› በማለት ነው የሚጠራው። ይህ ክፍል እግዚአብሄር አብን ‹‹አዳኛችን›› በማለት ሲጠራው፤ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ደግሞ ‹‹ተስፋችን›› በማለት ይጠራዋል።
2. የጢሞቲዎስ ተልዕኮ በቁ3 ላይ የሰፈረው ሰዎች የሃሰት ትምህርት እንዳያስተምሩ ማዘዝና በተጨማሪም በተረትና የትውልዶች ታሪክ በማውራት ጊዜአቸውን እንዳያባክኑ እንዲያዛቸው ነው። እነዚህን ሁለት ክፍሎች በማነጻጸር በአንድነት ስንመለከታቸው መረዳት የምንችለው ነገር ቢኖር፤ ጳውሎስ ለቤተ ክርስትያኒቱ ሽማግሌዎች ከመካከላቸው ለመንጋው የማይራሩ ተኩላዎች እንደሚነሱ በማስጠንቀቅ አስረግጦ የነገራቸው ነገር እንደተፈጸመ በግልጽ ማየት እንችላለን።
3. እኔ እንደምረዳው ከሆነ በቁ4-5 ውስጥ የተነገሩት በእምነት የሚሰራውን የእግዚአብሄር ሥራና በዚያው ክፍል የተጠቀሰውን ፍቅርን ማለቱ ሲሆን፤ ይህም ማለትም ስለ እምነትና ስለ ፍቅር መናገሩ ይመስለኛል። የእነዚህ የህግ አስተማሪዎች ትምህርት እንደ ከንቱ ንግግር ሆኖ በሐዋርያው የተነገረበት ምክንያት በ1ኛ ቆሮ 13 ላይ ‹‹ምስጢርን ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ…ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ›› ከሚለውን የእግዚአብሄር ቃል ጋራ የሚሄድ ሃሳብ ነው።
4. ሕግን በአግባብ መጠቀም ሲባ ለእኔ የሚገባኝ፤ ማንኛውም ነገር ለተፈጠረበት ሥራና አገልግሎት በትክክል ሲውል በአግባቡ በሥራ ላይ ዋለ ማለት እንደሚቻል፤ ለምሳሌ እርሳስ ለመጻፍ እንጂ ለጦር መሳሪያነት አልተሰራም፤ ወይም ደግሞ ቢላዋ መቆረጥ የሚያስፈልገውን ነገር ለመቁረጥ እንጂ ሰውን ለመውጋት አልተሰራም፤ እንዲሁም ህግን እግዚአብሄር የሰጠበትን ምክንያት በቁ9-10 ላይ ለሰፈሩት ዓይነት ነገሮች እንጂ ለሌላ ስላልሰጠ፤ ከዚያ ውጭ ቢጠቀሙበት መልካም አይደለም ማለቱ ነው። ጤነኛ ትምህርት የሚለው የእግዚአብሄርን ህግ እንደሆነ ነው የምረዳው።
5. ጳውሎስ ጌታን ከማወቁ በፊት ተሳዳቢ፣ አሳዳጅና አመጸኛ እንደነበረ ሲናገር፤ አሁን ግን የእግዚአብሄር ጸጋ ተትረፍርፎለት የአገልግሎት ሹመት የተቀበለ ሲሆን፤ ይህም የሆነበትን ምክንያት ሲናገር ባለማወቅና ባለማመን ያደረገው ነገር መሆኑን ይናገራል።
6. ጳውሎስ ራሱን ከሃጥያተኞች እንደ ዋነኛ አድርጎ ያያል። የጌታን ተልዕኮ እውነተኛነት ለማረጋገጥ የተጠቀመበት ተጨባጭ ሁኔታ የራሱን ደህንነት ሲሆን፤ የሐጥያተኞች ዋነኛ የሆነውን እርሱን ካዳነ በእርሱ ሊድን አይችልም የሚባል ማንም ሊኖር እንደማይችል ሲያረጋግጥ ነው።
7. ለጢሞቴዎስ የሰጠው ትዕዛዝ እርሱን፣ ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስን በመከተል መልካሙን ገድል እንዲጋደል ነው። መልካሙን ገድል ለመጋደል እምነትና በጎ ህሊና ያስፈልገናል። ሁለት መንገዶችን አያለሁ፤ እነርሱም የሚታዘዙት ከመንፈስ ቅዱስ፣ እንቢተኞች ደግሞ በሰይጣን ሊማሩ እንደሚችሉ አያለሁ።
8. ትክክለኛውን ትምህርት መከተላቸውና ከሃሰት ትምህርት የመራቃቸው ዋነኛ ዓላማና ግቡ ከንጹህ ልብ፣ ከበጎ ህሊና እንዲሁም ከእውነተኛ እምነት የሚገኝ ፍቅር እንደሆነ ሲሆን፤ ይህም ማለት አጥብቀን የያዝነው ጤናማ ትምህርት እግዚአብሄርንና ወንድሞቻችንን ወደ ማፍቀር የሚያደርሰን ሊሆን ይገባዋል እንጂ፤ ትክክለኛ የሆነ ትምህርት ይዘን በውስጡ ፍቅር ከሌለበትና ጌታንና ወገኖቻችንን ወደ ማፍቀር የማይመራን ከሆነ መጨረሻው ለትዕቢት ሊያጋልጠን ይችላል።

# ጥናት ሁለት 1ኛ ጢሞ 2፡1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በቅዱሳን ጉባኤ ጳውሎስ እንዲደረግ ጢሞቲዎስን የሚያዘው ነገር፤ ልመና፣ ጸሎት፣ ምልጃና ምስጋና እንዲደረግ ነው። እነዚህ ነገሮች እንዲደረጉ የሚያዘው ለሰዎች ሁሉ፣ ለነገሥታትና ለባለ ሥልጣናት በሙሉ ነው።
2. ከዚህ አነጋገሩ ለሰዎች ሁሉ፣ ለነገስታትና፤ ለባለስልጣናት ሁሉ መጸለይ ጳውሎስ እጅግ አስፈላጊና ዋነኛ ሥፍራ ሊሰጠው የሚገባ ትልቅ ነገር እንደሆነ ነው የምረዳው። ‹‹አሳስባለሁ›› የሚለው አነጋገር ሃሳብ እየሰጠ ወይም ምርጫ ያለን ነገር እንደሆነ አይደለም የሚገባኝ፤ ይህ አነጋገር ቀጥተኛ ትዕዛዝ መሆኑን ነው የማየው። ቅዱሳን ሁሉ እንደሚጠበቅብን በሥልጣን ላይ ለሚገኙት መሪዎችና አስተዳዳሪዎች ብንጸልይ ጌታ ነገሮችን የማይቀይርበት ምክንያት አይታየኝም፤ ለዚህም 2ኛ ዜና 7፡14ትን ማንበብ ይቻላል።
3. ምክንያት ሆነው ከተጠቀሱት መሃል ሶስቱ ብዬ የማያቸው፤ 1) በእውነተኛ መንፈሳዊ ህይወትና በቅድስና ሁሉ፤ በሰላምና በጸጥታ እንድንኖር፤ 2) ለነዚህ ሰዎች ሁሉ መጸለይ በእግዚአብሄር በአዳኛችን ፊት ደስ የሚያሰኝ ስለሆነና፤ 3) እግዚአብሄር ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን ወደማወቅ እንዲደርሱ ስለሚፈልግ የሚሉት ናቸው። እኔ ያየሁት በተለይም በሶስተኛነት የጠቀስነው የደህንነት ነገር ለሰዎች ሁሉ የሚፈልገው እንደሆነ ስለሚናገር በጸሎታችን ውስጥ የግድ ሊካተት ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ።
4. ይህ ክፍል በመጀመሪያ ደረጃ ኢየሱስን በእግዚአብሄርና በሰው መካከል እንዳለ አንድና ብቸኛ አስታራቂ አድርጎ ሲያቀርብልን፤ ለዚህ ሥፍራ ብቃቱን ስላረጋገጠበት መንገድ ሲነግረንም፤ ራሱን ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አድርጎ መስጠቱ እንደሆነ በቁ6 ላይ ይነግረናል። እኔ ከእነዚህ አነጋገሮች እንደምገነዘበው እግዚአብሄር ደህንነትን ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ያዘጋጀው ነገር እንዳልሆነና የሰው ልጆችን ሁሉ የሚጠቀልል ነገር እንደሆነ እመለከታለሁ።
5. ጳውሎስ በዚህ ቁጥር ላይ የራሱን ማንነት የገለጠባቸው ሶስቱ ነገሮች፤ የምሥራች አብሳሪ፣ ሐዋርያና ለአህዛብ የእውነተኛ እምነት አስተማሪ የሚሉት ናቸው። እነዚህን ሶስት ነገሮች ሐዋርያው የሚመለከትበት መንገድ እንደ ሽክምና የተጣለበት እዳ አድርጎ ሳይሆን፤ ከእግዚአብሄር የተሰጠው ሹመት አድርጎ ነው የሚያያቸው።
6. ስለወንዶች የተናገረው ነገር፤ በሁሉም ቦታ ያለቁጣና ክርክር የተቀደሱ እጆቻቸውን ወደላይ በማንሳት እንዲጸልዩ ሲሆን፤ ስለሴቶች ደግሞ በጨዋነትና ራስን በመግዛት ተገቢ የሆነ ልብስ እንዲለብሱ፤ በሹሩባ፣ በእንቁ ወይም ዋጋቸው ውድ በሆኑ ልብሶች እንዳይሽቀረቀሩና፤ በመልካም ምግባር እንዲዋቡ ያዛቸዋል። ለሴቶች ሁሉ ነው ብዬ አላምንም፤ ምክንያቱም በቁ10 ላይ ‹‹እግዚአብሄርን እናመልካለን የሚሉ ሴቶች›› ስለሚል የሚመለከተው እነርሱን ብቻ እንደሆነ አያለሁ።
7. ጸሐፊው ለጢሞቲዎስ የሚነግረውና ሴቶች በጉባኤ መሃል እንዲከተሉት የሚያዘው፤ በጸጥታና በሙሉ መገዛት እንዲማሩ፣ በተጨማሪም ሴቶች ዝም እንዲሉ እንጂ እንዲያስተምሩ ወይም በወንድ ላይ እንዲሰለጥኑ እንደማይፈቅድ ይነግረዋል፤ ለዚህም ምክንያት የሚለው በአንደኛ ደረጃ፤ አዳም አስቀድሞ መፈጠሩና ከዚያም ሔዋን መፈጠሯ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ የተታለለው ሔዋን እንጂ አዳም እንዳልሆነ ያስረዳል። 1ኛ ቆሮ 11፡3-16 ያለውን ክፍል ከዚህ ጋራ በአንድነት ማንበብ ይረዳል ብዬ አምናለሁ።
8. ሰዎችን ለማዳን የወሰዳቸውና እየወሰደ ያላቸው እርምጃዎች፤ ሂዱ ወንጌልን ለዓለም ሁሉ ስበኩ በማለት ሰራተኞች አሰማርቷል፣ በቁ1 ላይ እንደምናየው ቅዱሳን እንዲጸልዩ አዟል፤ አንዳንዶችን በህልም በመታየት፣ ለሌሎች ደግሞ በራዕይ ራሱን በመግለጥና በተለያዩ መንገዶች ሰዎችን ለማዳን ሲሰራ እናየዋለን።

# ጥናት ሶስት 1ኛ ጢሞ 3፡1-16 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የቤተ ክርስትያን መሪ ወይም ሽማግሌ ለመሆን በቅድሚያ የሚያስፈልገው ነገር ቁ1 እንደሚነግረን መፈለግ ወይም መመኘት ነው። የሰውየው የልቡ ፍላጎት ብቻውን በቂ እንዳልሆነ የምናውቀው፤ ከቁ2-7 ድረስ ይህ ለኤጲስ ቆጶስነት ፍላጎት የሚያሳየው ሰው በተጨማሪ ሊኖሩት የሚገባው ባህርያትና በክርስትና ህይወቱ በሰዎች ዘንድ ሊኖረው ስለሚገባው መልካም ህይወት ምስክርነት አስፈላጊነትና ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።
2. ኤጲስ ቆጶስ የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ በሥርዓት የሚኖር፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ማስተማር የሚችል፣ የማይሰክር፣ የማይጣላ፣ ጨዋ የሆነ፣ የማይጨቃጨቅ፣ ገንዘብን የማይወድ። ‹‹ማስተማር የሚችል ሲል መድረክ ላይ ወጥቶ የመስበክን ችሎታ ሳይሆን፤ የእግዚአብሄር ቃል እውቀት ያለውና ሰዎችን በተለያየ ሁኔታ ውስጥ ሲገኙ በቃሉ ሊመክርና ሊገስጽ የሚችል ማለቱ ነው። ገንዘብን መውደድ የሃጥያት ሁሉ ሥር ስለሆነ የማንንም ሰው ህይወት ሊያበላሽና ከመንገድ ሊያወጣ የሚችል ነገር ስለሆነ ነው።
3. ሰው ቤተ ክርስትያንን ማስተዳደር ሲፈልግ በቅድሚያ የራሱን ቤተሰብ በስርዓት ማስተዳደር መቻል አለመቻሉ ሊጠናና ሊረጋገጥ ያስፈልጋል። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተሰጡት ሁለቱ መመሪያዎች፤ አንደኛው አዲስ ክርስትያን እንዳይሆንና፤ ሁለተኛው ደግሞ በውጭ ባሉት ሰዎች ዘንድ ወይም ባላመኑት ዘንድ መልካም ምስክርነት ያለው ሊሆን ይገባል የሚሉት ናቸው።
4. የዲያቢሎስ ወጥመድ ሆኖ በዚህ ክፍል የቀረበው ነገር የአማኞች የህይወት ምስክርነት ማጣት ወይም ያላመኑ ሰዎች ስለ አማኞች የሚኖራቸውን አመለካከት ተጠቅሞ ምስክርነትን የማበላሸት ሥራውን ነው የሚያሳየን። አዲስ ክርስትያን ገና በአዲስነቱ በቤተ ክርስትያንን የማስተዳደር ሃላፊነት ሲሰጠው ዲያቢሎስ በአዕምሮው ሊጨምር የሚችለው እሱ ከሁሉ የበለጠና የተሻለ ስለሆነ አድርጎ ሊያሳየው ስለሚችል በቀላሉ መውደቅ ይቻላል።
5. በሁለቱም የቤተ ክርስትያን አገልጋዮች መመዘኛ ውስጥ የማያቸው የመጀመሪያው የአንዲት ሚስት ባል የሚለው (ቁ2 እና ቁ12)፤ ሁለተኛው ደግሞ ቁ4 እና ቁ12 ላይ የምናየው ልጆቻቸውንና ቤተሰባቸውን በአግባቡ ማስተዳደር የሚሉት ሃሳቦች ናቸው።
6. እንደ እኔ አመለካከት ከሆነ ይህ ክፍል የሚናገረው ስለሴት ዲያቆናት እንደሆነ እገምታለሁ፤ ይህንን ማለት የቻልኩበትም ምክንያት በመጀመሪያ ደረጃ የሽማግሌዎችን መመዘኛ ሲዘረዝር ስለ ሽማግሌዎች ሚስቶች ምንም የተናገረው ነገር ሳይኖር ስለ ዲያቆናት ሚስቶች ብቻ ለይቶ መናገሩ ትርጉም የለውም፤ ሌላ ደግሞ በሮሜ 16፡1 ላይ በቤተ ክርስትያን ውስጥ በዲያቆንነት የምታገለግለውን ፌቤንን እናያታለንና ነው።
7. የእግዚአብሄር ቤት የህያው እግዚአብሄር ቤተ ክርስትያን፣ የእውነት ዓምድና የእውነት ደግሞ መሰረት ብሎ ይጠራዋል። ለእውነተኛ መንፈሳዊ ህይወት ምሳሌ ሆኖ በቁ16 ውስጥ የቀረበልን ኢየሱስ ራሱ ነው።
8. ይህንን መልዕክት የጻፈበት ዋነኛው ምክንያት ሰዎች በእግዚአብሄር ቤት እንዴት መኖር እንዳለባቸው እንዲያውቁ ነው። ጳውሎስ ይህንን መልዕክት ማቆየት ያልፈለገበትና እስኪገናኙ ጊዜ ሊሰጠው ያልፈለገበት ምክንያት እኔ እንደገባኝ ከሆነ የመልዕክቱ አስቸኳይነት የታየውና መቆየት ያለበት ነገር እንደሆነ ስላላመነበት እንደሆነ ነው የሚመስለኝ።

# ጥናት አራት 1ኛ ጢሞ 4:1-16 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. አንደኛው የተነገረን ስለጊዜው ማለትም በኋለኞች ዘመናት እንደሚሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ይህ የሚሆነው ‹‹አንዳንዶች›› በተባሉት ሰዎች እንደሆነ፣ ሶስተኛው እነዚህ አንዳንዶች የተባሉት እምነትን እንደሚክዱ ሲሆን፣ አራተኛው ደግሞ ክደው ብቻ ሳይቀሩ መናፍስትንና የአጋንንትን ትምህርት እንደሚከተሉ እናነባለን፡፡ የዚህ ትምህርት ምንጭ ሆነው የተነገሩት፤ ህሊናቸው የደነዘዘባቸው ግብዝ ውሸተኞች በማለት በቁ2 ላይ ይናገራል፡፡
2. እነዚህ ሰዎች ከሚያስተምሯቸው መሃል አንዱ ሰዎች እንዳያገቡ ወይም ትዳር እንዳይኖራቸው ሲያስተምሩ፤ ሌላው ደግሞ የሚያምኑና እውነትን የሚያውቁ ሰዎች እግዚአብሄር የፈጠረውን በምስጋናም የሚቀበሉትን እንዳይበሉ ያዛሉ፡፡ የዚህ ዓይነት ትምህርቶችን ጳውሎስ የመናፍስትና የአጋንንት ትምህርት በማለት ነው የሚናገረው፡፡
3. በዚህ ክፍል ከተናገረው አነጋገር እግዚአብሄር ከፈጠረው ምግብ መሃል መብላት የማንችለው ምንም የለም ነው የሚለን፡፡ እንደ ጳውሎስ አነጋገር አማኝ ከእግዚአብሄር የሚሰጠውን ሁሉ በጸሎትና በምስጋና ስለሚቀበል፤ በዚህም ምክንያት ምግቡ ሁሉ የተቀደሰ ስለሆነ ለመብላት ድፍረት ይኖረዋል ማለት እንችላለን፡፡
4. ‹‹ይህንን ትዕዛዝ…›› ሲል በቁ1 ላይ መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስትያን እያስተላለፈ ያለውን መልዕክት የሚል ነው የሚመስለኝ፡፡ ጢሞቲዎስ ከዚህ ሊመጣ ካለው ነገር ራሱ እንዲጠነቀቅ ብቻ ሳይሆን ወንድሞችንም እንዲያሳስባቸው ነው የሚነግረው፡፡ ለእውነተኛ መንፈሳዊ ህይወት ራሱን ስልጠና ውስጥ እንዲያስገባ የተጠየቀ ሲሆን ለዚህ ደግሞ እንቅፋቶች፤ ርባና ቢስ አፈ ታሪኮችና፣ ከአሮጊቶች ተረታ ተረት እንዲርቅ ነው፡፡
5. እውነተና መንፈሳዊ ህይወትን ሲያነጻጽር የምንመለከተው ከአካል ብቃት ልምምድ ጋራ ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ሲነጻጸሩ ልቆ የሚገኘው ለእውነተኛ መንፈሳዊ ህይወት ራስን ማለማመድ ነው፤ ምክንያቱም ያኛው ለአሁኑ ብቻ የሚጠቅም ሲሆን መንፈሳዊው ግን ለአሁኑና ለሚመጣውም ህይወት ሁሉ እንደሚጠቅም ይነግረናል፡
6. በተለይም ቁ10ርን ስናነብ እነዚህ ጳውሎስና ጓደኞቹ በቁ7-8 ላይ ሌሎቹ እንዲለማመዱት ያስተማሯቸውን እውነት በራሳቸውም ህይወት ውስጥ በሥራ ላይ እንዲውል ‹‹እንጥራለን›› ‹‹እንደክማለን›› በማለት ይነግረናል፡፡ ይህ እግዚአብሄርን የመምሰል ልምምድ ቀላል ነገር ሆኖ አላየውም፤ ምክንያቱም ከጳውሎስ አነጋገር ብዙ ጥረትና ድካም የሚጠይቅ እንጂ በአንዴ የሚደረስበት ነገር እንዳልሆነ እንመለከታለን፤ ሆኖም በ2ኛ ጴጥ 1:3 ላይ እንደምናነበው ለዚህ ሁሉ ሃይል ስለተሰጠን የማይቻል ነገር አድርገን ልንወስደው አይገባንም፡፡
7. ወጣትነቱን እንዳይንቁት ካስፈለገ ጢሞቲዎስ ማድረግ የሚኖርበት ነገር ቁ12 እንደሚነግረን በንግግር፣ በኑሮ፣ በፍቅር፣ በእምነትና፣ በንጽህና አርአያ ሊሆናቸው ይገባል፡፡ ጢሞቲዎስ ከህይወቱ አርአያነት ባሻገር እንዲያዝና እንዲያስተምር (ቁ11)፣ በተጨማሪም ደግሞ እንዲያነብ፣ እንዲመክርና በማስተማር እንዲተጋ በቁ13 ላይ ያዘዋል፡፡
8. እነዚህ ጢሞቲዎስ ጥንቃቄ እንዲያደርግላቸው የተነገሩት ሁለት ነገሮች፤ የመጀመሪያው ለራሱ መንፈሳዊ ህይወት ጥንቃቄ ማድረግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ሌሎችን ለሚያስተምረው ትምህርት ምንነት መጠንቀቅ እንደሚኖርበተ ነው፡፡ ይህን የተባለውን ነገር ቢያደርግ በመጀመሪያ ደረጃ ራሱን ቀጥሎም ደግሞ የሚሰሙትን እንደሚያድን ከክፍሉ እንረዳለን፡፡

# ጥናት አምስት 1ኛ ጢሞ 5:1-25 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዚህ አይነቶችን ቃላት ሐዋርያው ሲጠቀም ጢሞቲዎስ የሚመራቸውን ህዝቦች በምን ዓይነት አመለካከት እንዲያያቸው፣ ማለትም እያንዳንዱን እንደራሱ ቤተሰብ አድርጎ እንዲያስብ ነው የሚነግረው። እነዚህን አራቱን አይነት የእድሜና የጾታ በአንድ ላይ ስንመለከት፤ ዛሬም በቤተ ክርስትያናችን የተለያዩ አይነት ሰዎችን ለማስተናገድ መዘጋጀትና አንዱን በምናስተናግድበት መንገድ ሁሉንም ማስተናገድ እንደሌለብን፤ እያንዳንዱን ሰው እንደማንነቱ ለማስተናገድ መዘጋጀት እንደሚኖርብን እንረዳለን።
2. በዚህ ክፍል መሰረት አማኝ እምነቱን በስራ ተረጎመ የሚባለው ወላጆቹን በሽምግልናቸው ሲረዳና ቤተሰቡን ሲደግፍ እምነቱን በሥራ ተረጎመ ይለናል። ቤተ ክርስትያን መበለቶችን የመደገፍ ሃላፊነት ቢኖርባትም፤ ማተኮር የሚኖርባት ልጆች ወይም የልጅ ልጆች በሌሏቸው ላይ ነው። እግዚአብሄር ደስ የሚሰኘው፤ አማኝ ቤተሰቡን በመደገፍ እምነቱን በሥራ ላይ ሲያውል ማየቱ ነው።
3. ቤተሰብን የመደገፍ ነገር ምርጫው ለእኛ የተተወ ነገር ሳይሆን እግዚአብሄር የደነገገው ትዕዛዝ አድርጎ ነው ጢሞቲዎስ እንዲያዛቸው የሚነግረው። ለዘመዶቹ በተለይም ለቅርብ ቤተሰቡ የማያስብና የማይረዳን ሰው ቃሉ ሲናገር፤ ሀይማኖቱን እንደካደ ሰውና፣ ከማያምን ሰው ይልቅ የከፋ እንደሆነ አስረግጦ ይነግረናል።
4. መበለት እድሜዋ ቢያንስ ስልሳ መድረስ ይኖርበታል፣ የአንድ ባል ሚስት ልትሆን ይገባል፣ ልጆች በማሳደግ፣ እንግዶችን በመቀበል፣ የቅዱሳንን እግር በማጠብ፣ የተቸገሩትን በመርዳትና ለበጎ ምግባር በሙሉ ራሷን በመስጠት በመልካም ስራ ሁሉ የተመሰከረላት መሆን አለባት፣ ወጣት ከሆነች በመዝገብ አትጻፍ። እኔ ከዚህ የማየው የጥንቷ ቤተ ክርስትያን የተደራጀና መስመር የያዘ የአሰራር ሥልትን ትጠቀም እንደነበረ እመለከታለሁ።
5. የመጀመሪያው ምክንያት ሆኖ የቀረበው፣ ሥጋዊ ፍላጎታቸው ሲያሸንፋቸው ለማግባት ይፈልጋሉ፤ ሁለተኛው ምክንያት ሥራ ፈት ሆነው ከቤት ቤት መዞር ይለምዳሉ፣ ሶስተኛው ደግሞ ሐሜትና በሰው ጉዳይ ጣልቃ የመግባትን ነገር ይለምዳሉ። ለእነዚህ ወጣት መበለቶች ምክሩ፤ እንዲያገቡና ልጆችን እንዲወልዱ፣ ቤታቸውን እንዲያስተዳድሩ፣ ከጠላት ነቀፋ እንዳይገኝባቸው በመሆን እንዲኖሩ ነው።
6. ይህ ቁጥር የሚነግረን ቤተ ክርስትያንን በሚገባ ስለሚያስተዳድሩና፣ ለሚያበራዩ፣ ለሚሰሩ፣ በተለይም በመስበክና በማስተማር ስለሚተጉ ሽማግሌዎች ነው። እነዚህ ሁለት ቃላት የሚጠቁሙን፣ ሽምግልና እንደ ሹመት ብቻ የሚወሰድ ነገር ሳይሆን በሚገባ ሌሎችን የሚያገለግሉበትና ይህም ደግሞ ትጋትን የሚጠይቅ ነገር እንደሆነ ነው የሚጠቁመን። በሬ የማበራየት ስራውን እየሰራ ከዚያው እንደሚበላ፤ እንዲሁም ወንጌልን በመስበክና በማስተማር የሚደክሙ ሰዎች ከቤተ ክርስትያን የሚገባቸውን እንዲሰጣቸው ማለቱ ነው።
7. የቤተ ክርስትያን ሽማግሌን ክስ ተቀባይነት እንዲያገኝ ካስፈለገ ከሁለት በላይ የሆኑ ምስክሮች ሊመሰክሩበት ያስፈልጋል፤ ይህ ሽማግሌ ደግሞ እውነትም በሃጥያት ከተገኘ በጉባኤ ፊት እንዲገሰጽ ጳውሎስ ያዘዘ ሲሆን፤ ይህም እንዲሆን የሚያስፈልገው ሌሎች ይህንን አይተው እንዲፈሩ ነው ይላል።
8. ጳውሎስ በዚህ ወጣት አገልጋይ እንዳይከሰት እየሰጋ ያለው ነገር በሰዎች መሃል አድልዎና ማበላለጥን እንዳያሳይ ነው። የጳውሎስን ማስጠንቀቂያ ጥብቅነቱን ሊያስረዳን የሚችለው ነገር የምለው ቁ21 ሲጀምር የሚጠራቸው የምስክር ብዛት ሲሆን፤ እግዚአብሄር አብን፣ ክርስቶስ ኢየሱስንና እንዲሁም የተመረጡትን መላዕክትም ሁሉ በመጥራት ነው አደራውን የሚያስተላልፈው።
9. አንደኛ ምእመናኑ ራሳቸው የቤተሰብነት ስሜት መስማት ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም በዚያው አይነት ማየት ይጀምራሉ፣ ሌላው ደግሞ ልክ በቁ21 ላይ የምናነበውን የማበላለጥና የአድልዎ ነገር ባያጠፋውም በብዙ ይቀንሰዋል፤ በተጨማሪ ደግሞ የቤተሰብነትን ነገር መረዳታቸው በፍቅር ለመመላለስ ምክንያት ይሰጣቸዋል።

# ጥናት ስድስት 1ኛ ጢሞ 6:1-10 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ቁጥር ላይ ምክር የሚጠው በባርነት ቀንበር ላሉት ነው። ምክንያት አድርጎ ጳውሎስ የሚሰጣቸው የእግዚአብሄር ስምና ትምህርቱ እንዳይሰደብ ነው የሚለው። ትዕዛዙ ለማንኛውም ባሪያ ለሆነ ሁሉ ሰው የተሰጠ ሳይሆን ለአማኞች የተሰጠ ትዕዛዝ ነው እላለሁ፤ ምክንያቱም፣ እንዲያደርጉ የተጠየቁበትን ምክንያት ስምመለከት በጌታ ላላመኑ ዓይነት ባሪያዎች ሊሰጥ የሚችል አይነት ስላልሆነ ነው።
2. በቁ1 ላይ ያሉት ያላመኑ ጌቶች ሲሆኑ፣ በቁ2 ላይ የምናያቸው ደግሞ አማኝ የሆኑ ጌቶች ናቸው። በብዙ ክርስትያኖች ዘንድ ሲከሰት የሚታየው ችግር፤ ክርስትያኖች አለቃቸው አማኝ መሆኑን ሲያውቁ የመዝናናትና የመናቅ ነገር ለማሳየት የመሞከር ችግር አለ፤ ሆኖም ጳውሎስ በዚህ ክፍል የሚናገረው፤ እንዲያውም አለቃህና ተጠቃሚው ወንድምህ ሲሀን የበለጠውን መልፋትና ማገልገል ይኖርባችኋል በማለት ነው የሚመክራቸው። እነዚህ ነገሮች ምክር ብቻ ሳሆኑ የእግዚአብሄር እውነት አድርጎ ተቀብሎ እንዲያስተምር ተነግሮታል።
3. ይህንን ትምህርት የሃሰት ትምህርት የሚያሰኙት ሁለት በቁ3 ላይ የተነገሩት ነገሮች፤ አንደኛው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጤናማ ቃል ጋራ ስለማይስማማና፣ ሁለተኛው ደግሞ እውነተኛ መንፈሳዊነትን ከሚያጎለብት ትምህርት ጋራ ስለማይስማማ ነው። ይህ ሰው በትዕቢት ተወጥሯል፣ አንዳች አያስተውልም፣ ለመከራከርና ለመጣላት ጉጉት አለው።
4. ይህ ክፉ ዘር የማያባራና የማያቋርጥ ንትርክን የሚመጣው ቁ5 እንደሚነግረን እውነትን በተቀሙ፣ መንፈሳ ነገርን ትርፍ ማግኛ አድርገው በሚቆጥሩ ሰዎችና፣ አዕምሮ በጎደላቸው ሰዎች መካከል እንደሆነ እናነባለን። እንደነዚህ አይነት ሰዎች መንፈሳዊ ነገርን በሰሩና ለእግዚአብሄር ኖረንለታል ብለው ባሰቡት መጠን እግዚአብሄር ደግሞ በዚያው መጠንና ከዚያም በላይ የመባረክ ግዴታ እንዳለበት አድርገው የሚቆጥሩ ሰዎች ናቸው።
5. እግዚአብሄርን መምሰል ማትረፊያ የሚመስላቸው ሰዎች እውነትን የተቀሙና አዕምሮ የጎደላቸው ሰዎች ሲላቸው፤ እግዚአብሄርን መምሰል ማትረፊያ የሚሆንላቸው ሰዎች ደግሞ ባላቸው ነገር የሚረኩ ሰዎች እንደሆኑ ይነግረናል።አንድ ሰው የልቡ መቃጠልና መሻቱ እውነተኛ እግዚአብሄርን መምሰል ከሆነ፤ ሌሎች የእግዚአብሄር ተጨማሪ በረከት ሆነው ከሚመጡ ነገሮች ላይ አይኑን በማንሳት እርካታው የእግዚአብሄርን ፊት በማየት ላይ ይሆናል።
6. ሰው ሁሉ ሊገነዘበውና በልቡ ጽላት ቢጽፈው የሚጠቅመው እውነት፤ ‹‹ወደ ዓለም ያመጣነው ምንም ነገር የለም፣ ምንም ነገር ይዘን መሄድም አንችልም›› የሚለው ነው ብዬ አምናለሁ። ሰው ይህንን እውነት እያሰበ ቢኖር በሰው ላይ ተረጋግጦ ገንዘብ መስራትን፣ ምንም ዋጋ ከፍሎ ገንዘብ ማካበትን እንደዋነኛ ተግባሩ አድርጎ አይመላለስም ነበረ ብዬ አምናለሁ። በምድር ላይ የሚያስፈልጉን ሁለት ነገሮች ምግብና ልብስ ናቸው።
7. ባለጠጋ ለመሆን የሚፈልጉ ሰዎች ወደ ፈተና ወደ ወጠመድ፣ ሰዎችን ወደ መፍረስና ወደ ጥፋት ወደ ሚያዘቅጠው ወደ ብዙ ከንቱና ክፉ ምኞት ይወድቃሉ። ‹‹ፈተና›› የሚለው የሚፈልጉትን ሃብት ለማግኘት ሲሉ የማይገባን ነገር ለማድረግ ይፈተናሉ፤ ‹‹ወጥመድ›› ደግሞ ብዙ ትብታብ ውስጥ ስለሚገቡ ከገቡበት ውስጥ ለመውጣት ስለሚቸገሩ ልክ ወጥመድ ውስጥ እንደገባ ወፍ ይሆናሉ ማለት ነው።
8. እነዚህ ሰዎች ከእምነት መንገድ የሳቱት ባለጠጋ ለመሆን ካላቸው ጉጉት የተነሳ እደሆነ ይነግረናል። በቁ6 ላይ የምናያቸው ሰዎች ባላቸው ነገር ረክተው የሚያተኩሩት እውነተኛ መንፈሳዊነትን በማዳበር ላይ ሲሆን፤ በቁ10 ላይ የምናያቸው ደግሞ ሌት ከቀን የሚያወጡትና የሚያወርዱት ባለጠጋ ስለመሆን ነው።

# ጥናት ሰባት 1ኛ ጢሞ 6፡11-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ‹‹አንተ ግን›› በማለት ጸሐፊው ጢሞቲዎስን የሚያነጻጽረው ቀደም ብለው ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ከተናገራቸው ባለጠጋ ለመሆን ጉጉት ካላቸውና ከዚህም የተነሳ በእምነታቸውም ሆነ በራሳቸው ላይ ጉዳት ካስከተሉት ሰዎች ጋራ ነው፡፡ ጢሞቲዎስ እንዲሸሽ የተነገረው ባለጠጋ ለመሆን ከመጓጓት ሲሆን፤ እንዲከታተል የተነገረው ደግሞ ጽድቅን፣ እውነተኛ መንፈሳዊ ህይወትን፣ እምነትን፣ ፍቅርን፣ ትዕግሥትንና ገርነትን ነው፡፡ ይህ ትዕዛዝ ለሁላችንም እንደሆነ የሚጠቁመኝ ሃሳብ ‹‹የእግዚአብሄር ሰው ሆይ›› የሚለው አነጋገር እኔንም ያካትታል ብዬ አምናለሁ፡፡
2. ጢሞቲዎስን የሚያበረታታው መልካሙን የእምነት ገድል እንዲጋደልና፤ የተጠራበትን የዘለዓለም ህይወት አጥብቆ እንዲይዝ ነው፡፡ በ2ኛ ጢሞ 4፡7 ላይ ጳውሎስ እሱ ራሱ ያላደረገውንና ያልተሸከመውን ሸክም በጢሞቲዎስ ጫንቃ ላይ እየጫነ እንዳልሆነ፤ ነገር ግን እርሱ ራሱ ይህንን ገድል ተጋድሎ እንደጨረሰ ጢሞቲዎስም የእርሱን ፈለግ እንዲከተል ነው የሚነግረው፡፡ ገድሉ ‹‹መልካም›› የተባለበት ምክንያት የሚያስገኘው በረከት ትልቅ ስለሆነ ነው፡፡
3. በዚህ ቁጥር ላይ እግዚአብሄር የቀረበው ‹‹ለሁሉም እውነትን የሚሰጥ›› በሚል ስያሜ ነው፡፡ አደራውን እንዲጠብቅ የታዘዘው በቁ14 ላይ እንደምናነበው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪገለጥ ድረስ ነው፤ ይህም የሆነበት ምክንያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተገለጠና እኛም ወደ እርሱ ከተሰበሰብን በኋላ የምንጋደለው ገድል ስለሌለ፤ በተጨማሪም እድፍና ነቀፋ ወይም ርኩሰት የሚባል ነገር በላይ በሰማይ ስለማይኖር ነው፡፡
4. የተባረከ፣ ብቻውን ገዢ የሆነ፣ የነገሥታት ንጉስ፣ የጌቶች ጌታ፣ ኢመዋቲ የሚሉት አያለሁ፡፡ ከእነዚህ ሁለት ጥቅሶች ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት የምንረዳው፤ እግዚአብሄር በራሱ ጊዜና በራሱ ሰዓት የሚያደርገው ነገር እንደሆነ እንመለከታለን፡፡
5. በቁ9 ላይ የተጠቀሱት ሰዎች ባለጠጋ ለመሆን የሚፈልጉ ሲሆኑ፤ በቁ17 ላይ የተጠቀሱት ሰዎች ግን ባለጠጎች የሆኑ ተብሎ ነው የተነገረላቸው፡፡ ጳውሎስ በቁ17 ላይ እንደሚናገረው የመጀመሪያ አደጋ በሌሎች ላይ የትዕቢትን ነገር ማሳየት ሲሆን፣ ሁለተኛው ነገር ደግሞ ከእግዚአብሄር ይልቅ ባላቸው ሃብት ላይ መታመን ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ገንዘቡ ከእግዚአብሄር የተሰጣቸው ነገር እንደሆነ እንረዳለን፡፡
6. ጳውሎስ ለባለጠጎቹ በቁ18 ላይ የሚያስተላልፈው መልዕክት፤ በገንዘባቸው መልካም ነገርን እንዲሰሩ፣ ቸሮች እንጂ ንፉጋን እንዳይሆኑ፣ ለማካፈል ፈቃደኞች እንዲሆኑ ነው፡፡ እኔ በአንድ በኩል ከነዚህ አነጋገሮች የምማረው፤ እግዚአብሄር ሲሰጠን ለራሳችን መጠቀሚያ ብቻ እንዳልሆነ ስረዳ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለሰዎች ብቻ እንዳልሆነና ለራሳችንም ደስታ ጭምር እንደሚሰጠንም እመለከታሁ፡፡
7. ቁ19 ላይ የምናነበው እውነተኛ ህይወት ብሎ እግዚአብሄር የሚጠራውን ህይወት ያገኛሉ፤ ለሚመጣውም ዘመን ጽኑ መሰረት የሚሆነውን ሃብት ለራሳቸው ያዘጋጃሉ ይለናል፡፡
8. ጢሞቲዎስ እንዲርቅ የሚነገረው እግዚአብሄርን ከማያስከብር ከከንቱ ልፍለፋና የውነት እውቀት ሳይሆን እንዲሁ በውሸት እውቀት ብለው ከሚጠሩት ዓይነት እውቀት ሲሆን ይህም የተቃውሞ ፍልስፍና እንደሆነ ይናገራል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ‹‹እውቀት›› እያለ የሚናገረው ጢሞቲዎስ እንዲሰብክ፣ እንዲያስተምርና ለታመኑ ሰዎች ሁሉ እንዲያስተላልፍ የተነገረው አይነት እውቀት ሳይሆን ‹‹የውሸት እውቀት›› እያለ ነው የሚጠራው፡፡ በዚያ መስመር የሄዱ ሰዎች መጨረሻቸው ከእምነት መንገድ መሳት እንደሆነ ቁ21 ያረጋግጣል፡፡
9. ጳውሎስ ባለጠግነትን የሚቃወም ሳይሆን ለጢሞቲዎስ በቁ11 ላይ እንደተናገረው እግዚአብሄርን ለማወቅና በእርሱ ለማደግ የሚደረገውን ጥረት የሚያስጥል ዓይነት የገንዘብ ፍቅር በልብ ውስጥ መለምለሙን የሚቃወም ነው፡፡